Date: December 17, 2007

# ከቅንጅት ሳውዝ ዳኮታ የድጋፍ ሰጭ ድርጅት

**ለቅንጅት ለአንድነትና ዲሞክራሲ ላእላይ መክር ቤት**

**አዲስ አበባ**

እኛ በሳውዝ ዳኮታና ባካባቢው የምንገኝ ኢትዮጵያውያን ከግንቦቱ ምርጫ ተከትሎ ወያኔ በህዝባችን ላይ የወሰደውን አረመኔያዊ ጭፍጨፋ በመቃወም የተሰባሰበን ኢትዮጵያውያን ስንሆን ያን ተከተሎ የህዝብ መሪዎች መታሰርና አፈናው ስለበዛ በቅንጅት ድጋፍ ሰጭነት ተደራጅተን የህዝባችን ምርጫ ለሆኑ መሪዎቹ መፈታትም ሆነ ባጠቃላይ የወያኔን ካህዲያዊ ስርአት ለማጋለጥ ኢትዮጵያዊ ግዴታችን ስንወጣ የነበረን ነን ። ሁላችንም ማለት ይቻላል የምንም አይነት የፖለቲካ ድርጅት አባል ያልነበርንና ቅንጅትን ከመሰረቱ ድርጅቶች ጋር ምንም አይነት ንክኪ የለነም ። ንጹህ የቅንጅት ደጋፊዎች ነን ። ይህን መገለጽ ያስፈለገን ከዚህ በታች ያስቀመጥነው አቓማችን ወገናዊ ያልሆነ ምስከርነታችን በፍጹም እውነት ላይ የተመሰረተ እና በበቂ መረጃ የተደገፈ ሆኖ እንዲወሰድልን ስለምንፈልግ ነው ።

እኛ በሳውዝ ዳኮታ የምንገኝ የቅንጅት ደጋፊዎች የቅንጅት አባላት በሙሉ ለተሻለ ስርአትና ዲሞክራሲን አገራችን ላይ ለማምጣት ፍጹም ጨካኝ ከሆነው አንባገነን መሪ ነኝ ባይ መለስ ዜናዊ እና ከማፊያ ድርጅቶቹ ጋር ያረጋቸሁትን ትግል የከፈላችሁትን መሰዋትነት እጅግ ያደነቅነውና ክብር የሰጠነው ነው ።

እኛ በሳውዝ ዳኮታ የምንገኝ የቅንጀት ደጋፊዎች ከእስር ለተፈቱ የቅንጅት ከፍተኛ አመራር አባላት እኩል የሆነ ከበሬታ እና ፍቅር አለን

እኛ በሳውዝ ዳኮታ የምንገኝ የቅንጅት ደጋፊዎች ቅንጅትን ስንደግፍ ቅንጅት ለዲሞክሪያሲያዊ ስርአት የሚታገል አባላቱም በዲሞክራሲያዊ ስርአት እሴቶች የሚኖሩ ተግባራቸውም አንደበታቸው በዚሁ የተሞላ ነው ብለን አምነን ነው ።

በርግጥም የሚገርም አስተዋይነት ትህትና ትግስት ቆራጥነት ያላቸው ሆነው አግኝተናቸዋል ። በይበልጥም ከአመራር አካላቱ በአካል ልናያቸው የቻልነው ምክትል ሊቀመንበር ወ/ሪ ብርቱካን ሚደቅሳ እና እንጂነር

ግዛቸው ሽፈራው  በሳውዝ ዳኮታ እና ባካባቢው ኢትዮጵያዊ ነዋሪዎች
ላይ ከፍተኛ ፍቅርን ጥለውብን ነው የሄዱት ከፍ ያለ አክብሮትም
እንድንሰጣቸው አርገውናል ፡፡

እኛ በሳውዝ ዳኮታ የምንገኝ የቅንጅት ደጋፊዎች በቅንጅት አመራር አካልት ሙሉ
መተማመኑ ስላለን ባሁኑ ሰአት በቅንጅት ውስጥ የተፈጠረውን ችግር የመፈታት
ችሎታውም ተሞክሮውም አላችሁ ብለን እናምናለን
ያ እንደተጠበቀ ሆኖ እኛ በሳውዝ ዳኮታ የምንገኝ የቅንጅት ደጋፊዎች በአቶ ሀይሉ
ሻውል ደብዳቤ ያለን አቋም  ከሀላፊነትና ከስራ ድርሻቸው አኩዋያ
እንዳናከብራቸውና በዚህ መንገድ ልንገልጻቸው በፍጹም የማንፈልጋቸው የቅንጅቱ
ሊቀመንበር አቶ ሀይሉ ሻውል በፍጹም አንባ ገነን ሆነው አግኝተናቸዋል፤

ለዚህም ያምባገነኖች መገለጫ የሆኑትን ውይም መለያ ገጸ ባህርያት የተላበሱ
መሆናቸው ባማያጠያይቅና በማያዳግም በተደጋጋሚ አይተንባቸዋል ፡፡

1ኛ- በራስ አለመተማመን - በብዙ ንግግሮቻቸው ወይም ቃለ መጠይቆቻቸው
ስልጣኔን ሊቀሙኝ እየዶለቱ ነው የሚል እድምታ ያለው ሆኖ አግኝተንዋል ፡፡

እ.ኢ..አ. በታህሳስ 1/ 2000 ዓ.ም የወጣው መግለጫቸውም በሙሉ በዚሁ ባዶ ፍራቻ
የተሞላ ሆኖ አግኝተንዋል ፡፡ ለፍራቻቸው ምክንያት የሆነውን ነገር ግን ፈልገን
አፈላልገን ማግኘት አልቻልንም ፡፡ ስልጣን አብዝቶ ከመውደድ የሚመጣ ሆኖ ብቻ
ነው ያገኘነው

2ኛ- በውሸት መሞላትና በትቢት መወጠር - ከእስር ከተፈቱ ጀምሮ በተለታየ
ራዲዮች እንዲሁም በመወያያ መድረኮች ላይ ያደረጉዋቸውን ደርዘን የሚሞሉ ቃለ
መጠይቆች የተከታተልን ሲሆን የጤንነታቸው ሁኔታ እስኪያጠራጥረን በውሸት
የተሞሉ እና የተምታቱ ትቢተኛ ሆነው አግኝተናቸዋል ፡፡

3ኛ- ያምባገነኖች ዋንኛ መገለጫ የሆነው ንቀትና ተሳዳቢነት በእስር ላይ እያሉም ሆነ
ከተፈቱ በሁዋላ የወሰኑዋቸው ውሳኔዎች አንዱም የኢትዮጵያን ህዝብ እና የቅንጅት
ደጋፊዎችን በይበልጥም የስራ ባልደረቦቻቸውን መኖር እና ስሜት ግምት ውስጥ
ያስገባ ያከበረ ሆኖ አላገኘነውም፡፡ እንዳውም ከበታቻቸው ላሉ የቅንጅት አመራር
አካላት ከመነሻው ያሳዩ የነበረው ንቀትና የሚጠቀሙባቸው የስድብ ቃላት የህዝብ
ተመራጮች መሆናቸውን ያላገናዘበ ፍጹም ንቀትና በብልግና የተሞላ ሆኖ
አግኝተንዋል፡፡

4ኛ- ቡድናዊነት ወገናዊነት ውሳኔያቸው ንግግራቸው ድርጊታቸው በሙሉ የኔ የሚሉትን ለመጥቀም የሚያረጉት መሆኑን ለማወቅ በጣም ቀላል ሆኖ ነው ያገኘነው። በግልጽ ለኔ ወገን እያሉ ሲናገሩ መስማት የተለመደ ነው፤

5ኛ- እነዚህ ከብዙ በጥቂቱ ሲሆኑ ከዳተኝነት ፤ እኔ ያልኩት ካልሆነ ባይነት፤ የተለየ ክብር ለምን አልተቸረኝም ፤ እራስ ወዳድነት ፤ ጭካኔ ፤ የበዛ ጥላቻ የሰፈሩባቸው መሆንቸውን ማየት ማዳመጥ ቸለናል። ይህንን ለማረጋገጥ አቶ ሀይሉ ሻውል ዲሲ ላይ ከህዝብ ጋር ያረጉትን ስብስባ እንደመረጃ ለመጠቀም ይቻላል ዘንድ ላእላይ ምክር ቤቱ ቪዲዮውን እንዲያይ እንጠይቃለን። ይህ ቪዲዮም ኢቲን የኢትዮጵያ ቴሌቪዥን ኔትወርክ ይገኛል፤

እነዚህን እላያቸው የሚታዩ መጥፎ ባህርያት ምን አልባት ከጤናቸው እና ከድሜ ጋር ተያይዞ የመጡ ወይም በእስር ቤት ያሳለፉት የመከራ ጊዜያቶች ያሳደሩባቸው ሳይኮሎጂካል ቸግሮች ሳይሆኑ አይቀሩም የሚል ከፍተኛ ጥረጣሬ አለን ጤናቸውን በተመለከተ ያላቸው የጤና ሁኔታ በፍጹም ለመሪነት ብቁ እንደማያረጋቸው ዲሲ ላይ ባደረጉት ስብሰባ አይተናቸው አውቀናል የማየትና የማንበብ የመስማትና የማዳመጥ የማገናዘብ ችግሮች እንዳሉባቸው ግልጽ ብሎ ይታያል። እነኝህና የመሳሰሉ ሌሎች ችግሮቻቸውና ባህሪያቸው ከሌላ ከሶስተኛና የውጭ አካል መረጃና ትርጉም ትንተናና ገለጻ እንዲያገኙ ስላረጋቸው አስተሳሰባቸውን እለት ተእለት እየጎዳው በመሄዱ በባህሪያቸው ላይ ተጽኖ ከማድረሱም አልፎ በውሳኔዎቻቸው ላይ ፍጹም አምባገነን አድርጋቸዋል።

እኛ በሳውዝ ዳኮታ የምንገኝ የቅንጅት የድጋፍ አባላት ከላይ በተጠቀሱት እና በሌሎቸም ምክንያቶች እንደ ኢትዮጵያ አቆጣጠር ታኅሳስ 1 ቀን 2000 ዓ.ም ለቅንጅት ለአንድነትና ዲሞክራሲ ላእላይ ምክር ቤት አቶ ሀይሉ ሻውል የላኩትን ደብዳቤ እስከነ ሙሉ ይዘቱ  ውድቅ ያደረግነው መሆኑንና የማንቀበል መሆናችን አበክረን እንገልጻለን።

1ኛ- የተዘረዘሩት ክሶች በሙሉ በፍጹም ውሸት ሆነው አግኝተናቸዋል፤ ነገር ግን በቁጥር ሁለት ከተመለከተው በስተቀር ያም እስር ቤት እያሉ ስለተፈጠረው ጉዳይ ላቀረቡት ውንጀላ በኛ በኩል መርጃውም ወይም እውቀቱ ስለሌለን ነው

2ኛ- ውሳኔዎቻቸው በሙሉ ፍጹም አንባገነናዊ ስርአትን የተላበሱና በምንም መልኩ የቅንጅትን ደንብና ስርአት ያልተከተለ ሆኖ አግኝተናቸዋል

3ኛ- ደብዳቤው ጊዜ ተወስዶ ያልተጻፍ የደብዳቤው ፀሀፊ አቶ ሀይሉ ሻውል ይሁኑ ወይም ከአንድ በላይ በሆኑ ሰዎች የተጻፈ የሚመስል እኔ እና እኛ እያለ የሚያምታታ ሆኖ አግኝተነዋል። እንደ አጼ ሐይለ ስላሴ እኛ እያሉ እራሳቸውን መገለጽ የጀመሩ

አስመስሎአችዋል፤ ይህም ደግሞ ሌላው ችግራቸውና ለኢትዮጵያችን ለህዝባችን የማይጥቅም ከመሆኖም አልፎ አንድ ርምጃ ወደፊት ይማያስኬድ ከፋፋይ ርዝርዥ ስርአት ነው፤ ከእንግዲህ ማንም ይሁን ምንም በሌላው ትክክ መኖር አይችልም፤

4- የአዋጁ ነጋሪም ሆነ ፀሀፊ የቅንጅት ሳውዝ ዳኮታ አባል የነበረ እና ለወያኔ እንደሚሰራ ሲታወቅበት ከአስራ ስምንት ወር በፊት የሸሸና ስራ ካቆመ የቆየ ግለሰብ መሆኑ የበለጠ አናዳጅ ሆኖ አግኝተንዋል ።

<u>መፍትሄ</u>

1ኛ- የቅንጅት ላእላይ ምክር ቤት ለዚህ ሰጣ ገባ እልባት መስጠት ያልቻለበትን የስካሁን ችግሮች የምንረዳ ሲሆን ይህ ቸግር በድርጅቱ ሀልውና ላይ ከጣለው አደጋ አኩዋያ ማንኛውንም የላእላይ ምክር ቤት አባል ከምንም ቡድነኛነት ወገናዊነት በጸዳ መንገድ ችግሩን አይተው ወደፊት ሊያስኬድ የሚቸል ውሳኔ በአስቸኩዋይ እንድትሰጡ በኢትዮጵያ ሕዝብ ስም እንጠይቃለን።

2ኛ- ውሳኔያቸሁ ፍጹም ዲሞክራሲያዊ ስርአትን የተከተለ እንዲሆን እንጥይቃለን

3ኛ- ውሳኔያችሁ አሮጌ ሱሪ ላይ ጨርቅ መጣፍና ድሪቶ መደረት ይብቃን ይሆን ዘንድ አበክረን እንጥይቃልን

4ኛ- ውሳኔያችሁ ሁሉን አቅፍ ፍትህዊና ወደፊት የሚያስኬድ ውሳኔና ስኬታማ ይሆን ዘንድ ሁሌ ፈጣሪን በመለመን በጸሎት ስብሰባችሁን ትጀምሩ ዘንድ እንጠይቃልን

ከቸግሩ ጀርባ እጃቸው ያለ ድርጅቶች ከችግሩ እሳት ላይ ጭድ ጨማሪዎች
እኛ በሳውዝ ዳኮታ የምንኖር የቅንጅት ድጋፍ ሰጪ አባላት ከዚህ በታች የተዘረዘሩ ድርጅቶች እና ግለሰቦች በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ዛሬ ቅንጅት ውሰጥ ለተፈጠረው ችግር ተጠያቂዎች ናቸው ብለን እናምናለን ። ይህን በማድረጋቸው በጣም አዝነናል።

የወያኔ እድሜ እንዲራዘም የሂወት መሰዋትነት የተከፈለበት ትግል አሁንም በድጋሚ መና ሆኖ እንዲቀር አድርገዋል ። ግለሰቦቹም ሆኑ ድርጅቶቹ ከዚህ በፊት ሂወት የጠፋበት ትግል መና ሲሆን ያዩ የነበሩበት መሆኑን ስናስበው ደግሞ አንገታችንን ያስደፋናል። ይህን ዝርዝር መግለጽ ያስፈለገን የላእላዩ ምክር ቤቱ በቅንጅት ውስጥ የተፈጠረውን ችግር በዝቶ ከመራገቡ አኩዋያ የችግሩን ፌሬ ነገር ለመያዝ ለማወቅ ያለባቸውን ችግር ተገንዝበናል ይህ የኛም የሁሉም ኢትዮጵያዊ ችግር ስለሆነ የቅንጅት ላእላይ ምክር ቤት መፍትሄ ፍለጋና ለውሳኔያችሁ በሚያረጉት ጥረት ችግሩን ከሌላ አቅጣጫም ለማየት ትንሽ ችግር ሆኖ የተወሳሰበበትን ሁኔታ ለማየት

ያስችላቸዋል ብለን ስላመን ነው ።

1ኛ- ለዚህ ሁሉ ችግር የንጹሀን ደም የፈሰሰበት የቅንጅት ትግል እንዲዳከም ዶ/ር ታዬ ወልደ ሰማያት እና ግብራበሮቹ መቶ ፐርሰንት ተጠያቂ እናደርጋቸዋለን

2ኛ- የእያሱ አለማየሁ ኢህአፓ መገናኛ የሆኑት ድህረገጾች ኢትዮ ላዮን፤ ደብተራው አሲምባ እንዲሁም በዚሁ አንጃ ሰዎች የሚመሩ የመወያያ መድረኮች ከዚህ ጋር የተያያዙ ግለሰቦች ነገሮችን በማራገብ የውሸት አሉባላታ በማስወራት ለችገሮቹ በቂ ድርሻ እንዳላቸው እንመሰክራለን። ለዚህም የቅንጅት የውስጥ ጉዳይ ውስጥ ጣልቃ መግባቱ ከሌሎች ምክንያቶች በዝቶ የህዝብ ድርጅት የሆነውን ኢህአፓ ንም እስከመክፈል መድረሱ የሚታወቅ ነው ።

3ኛ- ህብረቱ የተለያየ ድርጅት ጥምር ቢሆንም ሁሉም በተናጠል ያላቸውን አቋዋም ባናውቅም በጋራ ለመስራት እንደመስማማታቸው በሰው ደም መሰዋትነት የተከፈለበት የህዝብ ትግል ላይ የዚህ አይነት ደባ ሲሰራ ለመቃወምም ለመከላከልም ቤቱን እንደህብረትነቱ ስረአት ለማስያዝ አለመቻሉ ተጠያቂ ያረገዋል

4ኛ- ወያኔ በራሱም ቅንጅት ውስጥ ለተፈጠረው ችግር ቀንደኛው አካል ሲሆን ከወያኔ በኩል ያለው የተጠበቀ ስለሆነ ነው መሰለን ጣልቃ ገብነቱ እስካሁን በዝቶ አልታየም።

እኛ በሳውዝ ዳኮታ የምንገኝ የቅንጅት ድጋፍ ሰጪ አካላት ለማንኛውም ኢ-ዲሞክራሲያዊና ስርአት አልበኝነት አካላት የህዝብን ትግል ለማደናቀፍ የሚደረግን ደባና ፈጻሚዎች መለስ ዜናዊ እና ግብራበሮቹን በምንዋጋበት በምናይበት ሀይል እና ፍላጎት እንደምንታገል ግልጽ ማረግ እንፈልጋለን ።

የሳውዝ ዳኮታ ቅንጅት ድጋፍ ሰጭ
ሱፎልስ፤ ሳውዝ ዳኮታ

<u>ግልባጭ</u>
ለቅንጅት የሰሜን አሜሪካ የደጋፍ ድርጅቶች አስተባባሪ
ለቅንጅት ቻፕተሮች በሙሉ በያሉበት
ለማንኛውም ድህረገጽ ወይም ሜዲያ